የሰ/መ/ቁ. 111960

ህዳር 06 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዐ/ህግ - አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** ሰይፈ አበበ ንጉሴ - በሌለበት ታይቶ የተወሰነ በመሆኑ አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአሁኑ አመልካች ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ተከሳሽ (ተጠሪ) አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 በመተላለፍ የኮንትሮባንድ እቃ የጉምሩክ ስርዓት ያልተፈጸመበት መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ እያለበት 21 ጀሪካን ዘይት ቀረጥና ታክስ መጠኑ በአጠቃላይ ብር 6025.45 (ስድስት ሺህ ሃያ አምስት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም) የሆነ በመኖሪያ ቤት ውስጥ ሽንት ቤት ክፍል ውስጥ ተከማችቶ እጅ ከፍንጅ ስለተያዘ የኮንትሮባንድ እቃ ይዞ በመገኘት ወንጀል ፈጽሞ ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ፍቃድ እያለኝ ከእኔ ላይ የተያዘው ስለሆነ ህጋዊ ነኝ ጥፋት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ከሳሽ የአሁኑ አመልካች የሆነው ዐቃቤ ህግ ሁለት ምስክሮችን ያሰማ ሲሆን ተከሳሽም ሁለት መከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አስመስክሯል፡፡ የጽሁፍ መከላከያ ማስረጃ በቀን 30/01/2004 ዓ/ም የተሰጠ እስከ 2007 ዓ/ም የታደሰ የምግብ ዘይት የንግድ ፈቃድ ተከሳሽ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽን (የአሁኑ ተጠሪን) ተከላክሏል በማለት በወንጀል ስነስርዓት ህግ ቁጥር 149(2) መሰረት በነጻ እንዲሰናበት በማለት የአሁኑ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ በወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 195(1) መሰረት በመ/ቁ.200935 በቀን 01/07/2007 ዓ/ም ዘግቷል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው። የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡-

1. የስር ፍርድ ቤቶች በጅምላ ተጠሪው የታደሰ የንግድ ፍቃድ መኖሩን በማረጋገጡ ብቻ ከኮንትሮ ባንድ ወንጀል ሃላፊነት ያድናል ማለት መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት ነው፣
2. የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 መሰረት ማንኛውም ስሪት ሃገሩ የውጪ የሆነ እቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት በነጻ ዝውውር እንደማይለቀቅ በግልጽ ተደንግጓል። ተጠሪው ከኮንትሮ ባንድ ወንጀል ሃላፊነት ነጻ ለመሆን ለእቃው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን የሚያስረዳ የእቃው ጉምሩክ ዲክላራሲዮን (ሰነድ) የማቅረብ ህጋዊ ግዴታ እያለበት የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው ታክስ ከፍሎ ንግድ ፍቃድ አውጥቷል በማለት በነጻ ማሰናበታቸው የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልን እንጠይቃለን የሚል ነው።

አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል። ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ትዕዛዝ ተሰጥቶ አመልካች ተጠሪን ፈልጎ ያለማግኘቱን ገልጾ ጥሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲደረግ ጠይቋል። በዚሁ መሰረት ሀምሌ 6 ቀን 2007 ዓ/ም በታተመ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ ስላልቀረበ በሌለበት ታይቶ እንዲወሰን ትዕዛዝ ተሰጥቷል።

የክርክሩ ሂደት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ጉዳዩን ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ፤አመልካች ካቀረበው አቤቱታ እንዲሁም አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነውም በተጠሪ መኖሪያ ቤት ውስጥ በሚገኘው ሸንት ቤት ውስጥ በክሱ የተጠቀሰው 21 ጀሪካን ዘይት ተይዟል። በክሱ ውስጥ የተጠቀሰ መጋዘን እየታደሰ ዘይቱ አዲስ ሸንት ቤት ውስጥ ከሌሎች የሱቅ እቃዎች ጋር መገኘቱን የከሳሽም ሆነ የተከሳሽ ምስክሮች በተመሳሳይ ሁኔታ መስክረዋል። ተከሳሽ (ተጠሪ) በ2004 ዓ/ም የተሰጠ የዘይት ንግድ ፍቃድ እስከ 2007 ዓ/ም ድረስ የታደሰውን ማቅረቡ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጧል። የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ተከላክሏል በማለት በነጻ አሰናብቷል። በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 መሰረት ተጠሪው ከተከሰሰበት ወንጀል ሃላፊነት ነጻ ለመሆን ለእቃው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን የሚያስረዳ የዕቃው ጉምሩክ ዲክላራሲዮን (ሰነድ) የማቅረብ ህጋዊ ግዴታ እንዳለበት

ተመልክቷል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪው የዘይት ንግድ ፈቃድ አለው ከመባሉ በስተቀር ዘይቱን ከማንና ከየት እንደገዛ እንዲሁም ለገዛበት ዘይት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መክፈሉን የሚያስረዳ የእቃው ጉምሩክ ዲክላራሲዮን (ሰነድ) ተጠሪ አቅርቦ አላረጋገጠም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ተጠሪ ተከላክሏል ለማለት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሆኖም ግን አከራካሪ ሆኖ የታየው ተጠሪ በተከሰሰበት አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 "ህገ ወጥ እቃዎች ይዞ ስለመገኘት" ተብሎ የተደነገገው ድንጋጌ ይህን አዋጅ በተካው በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ላይ ወንጀል ሆኖ ተደንግጓል ወይስ አልተደነገገም? የሚለውነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ላይ አልተደነገገም፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 168 የተደነገገው "የኮንትሮ ባንድ ወንጀል" በሚል ነው፡፡ ይህም በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ የተደነገገነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 የተደነገገው በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ካልተደነገገ ህጋዊ መፍትሔ (legal remedy) ምንድነው? የሚለው ምላሽ ሊያገኝ ይገባል፡፡ ይህ አዋጅ ግን ይህንን ጥያቄ የሚመልስ የህግ መርህ አይደነግግም፡፡ በዚህ ጊዜ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት የተደነገገው መሰረታዊ መርህ እንዲሁም በወንጀል ህጉ በመርህነት የተደነገገው ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በሌላ አነጋገር በኢፌዲሪ ህገ መንግስትና በወንጀል ህግ ከተደነገገው መሰረታዊ መርህ አንጻር ታይቶ መተርጎም ይኖርበታል፡፡ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 22 የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 5 በተመሳሳይ መልኩ ደንግጎታል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22(2) ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ የወጣ ህግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኃላ የወጣ ህግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል በማለት ተደንግጓል፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 5(3) የተሻረው ህግ ይሰራ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመ ወንጀል ሲኖርና በዚህ ህግ ግን እንደወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን ሊያስከሰስም ሆነ ሊያስቀጣ አይችልም፤ ክሱም ተጀምሮ እንደሆነ ይቋረጣል ተብሎ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የፈጸመው ድርጊት ምንም እንኳን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 ላይ ወንጀል ሆኖ የተደነገገ ቢሆንም በዚህ አዋጅ ምትክ በተተካው አዋጅ ቁጥር 859/2006 ወንጀል ሆኖ አልተደነገገም፡፡ ስለዚህ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት እና በወንጀል ህጉ በተደነገገው መሰረታዊ መርህ አንጻር ሲደመደም ተጠሪ ጥፋተኛ ተደርጎ ቅጣት የሚወሰንበት የህግ አግባብ የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 44610 በቀን 22/04/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 200935 በቀን 01/07/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ከላይ በፍርድ ሀተታው የተገለጸውን የኢፌዲሪ ህገ መንግስቱንና የወንጀል ህጉን መሰረታዊ መርህ መሰረት ያደረገ ባይሆንም በውጤት ደረጃ ግን ልዩነት ስለሌለው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 195(2) (ለ) (2) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤትይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

# ውል